# አብዮታዊ ዴሞክራሲ (ጥር 3/1998 ቁጥር 198)


- ኢህአዴግ የሃገሪቱን ሰላምና ልማት ለማጎልበት የተጠናከረ ስራ እንደሚሰራ ገለፀ - ገፅ 1
- ፀረ-ድህነት ትግል ውስጥ የምሁራን ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ተገለፀ - ገፅ 3
- ኢትዮጵያ በ5 ወራት ከ1 ቢሊዮን ብር በላይ የውጭ ሃብት አግኝታለች - ገፅ 4
- አሁንም ህዝብና መንግስት እጅና ጓንት ናቸው - ገፅ 5
- ጠንካራ ውስጣዊ ልማት ለአበረታች የውጭ ድጋፍ - ገፅ 7
- የውጭ ድጋፍ ለሃገር ውስጥ ልማት - ገፅ 8
- እያንዳንዷ ቀን ለሰላምና ለልማት - ገፅ 11


## ዜና

## ኢህአዴግ የሃገሪቱን ሰላምና ልማት ለማጎልበት የተጠናከረ ስራ እንደሚሰራ ገለፀ

የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ባለፉት 3 ወራት በሁሉም አካባቢዎች የተረጋጋ ሁኔታ እንዲፈጠር የተሰሩትን የተሳኩ ስራዎች መሰረት በማድረግ በቀጣይም የሃገሪቱን ሰላምና ልማት ለማጎልበት የተጠናከረ ስራ መስራት እንደሚኖርበት ወሰነ፡፡

የኢህአዴግ ቃል አቀባይ እንደገለፀው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ታህሳስ 28 ቀን 1998 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ባለፉት ወራት የነውጠኛ የቅንጅት መሪዎች፣ አነግና ሻዕቢያ በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ሰላምና ልማትን ለማወክ የተደረጉትን ሙከራዎች ለማክሸፍ የተከናወኑት ስራዎች ተገቢ እንደነበሩ በመገምገም ወደፊትም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ወስኗል፡፡

ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰላምና መረጋጋትን ከማረጋገጥ ጎን ለጎን የልማት እቅዶች ሳይደናቀፉ እንዲቀጥሉ በማድረግ በኩል የተሰሩት ስራዎችና የተገኙት ውጤቶችአበረታች እንደሆኑ በተለይም ደግሞ በግብርና ምርት ረገድ ዘንድሮም አጥጋቢ ምርት የሚገኝበት ሁኔታ እንዳለ አረጋግጧል፡፡

በግብርናው መስክ በበጋውና በቀጣይ ክረምት የተጠናከረ የልማት እንቅስቃሴ እንዲደረግና በተለይም ምርታማነትን ለማሳደግ የላቀ ትኩረት እንዲሰጥ ስራ አስፈፃሚው መወሰኑን ቃል አቀባዩ አስታውቋል፡፡

በሌላም በኩል በከተሞች የስራ አጥነትና የመጠለያ ችግሮችን ለመፍታት የተቀናጀ የልማት ፓኬጅ ለማዘጋጀት የተጀመረውን ጥናት በፍጥነት በማጠናቀቅ ወደተግባር የሚገባበት ሁኔታ እንዲፈጠር ስራ አስፈፃሚው ወስኗል፡፡

የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው መልካም አስተዳደርን ከማጎልበት አኳያ በተለይም በወረዳና በቀበሌ አስተዳደር እንዲሁም በመንግስት ሰራተኞች አስተዳደርና በፍትህ ስርዓቱ ዙሪያ የሚታዩ የአደረጃጀትና የአሰራር ችግሮችን ለመፍታት የተጀመረውን ጥናት አጠናቆ በፍጥነት ወደ ተግባር መግባት እንደሚያስፈልግ መወሰኑን ቃል አቀባዩ ጠቁሟል፡፡

የአገራችን ህዝቦች በየደረጃው በሚከናወኑ የሰላም፣ መልካም አስተዳደርና የልማት ተግባራት ዙሪያ የሚኖራቸው ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲዳብር በማድረግ በኩል የተጀመሩት ጥናቶችና የተገኙት ውጤቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ማድረግ ወሳኝ እንደሆነ ስራ አስፈፃሚው ተመልክቷል፡፡

በዚህ ረገድ ከምሁራን፣ ወጣቶች፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣ የከተማ ነዋሪዎች፣ አርሶ አደሮች በአጠቃላይም ከህዝቡ ጋር በመመካከር የአገራችንን ችግሮች በዘላቂነት የሚፈቱ ተግባራትን ለማከናወንና በህዝቡ ውስጥ የዳበረ ፖለቲካዊ ስራ ለመስራት የተያዘውን መልካም ጅምር አጠናክሮ መቀጠል እንደሚያስፈልግ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ ማስተላለፉን ቃል አቀባዩ አስረድቷል፡፡

የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ቀደም ሲል የነበሩትን ጉድለቶች በማስተካከል የኢህአዴግን ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ስራ በተጠናከረ መንገድ ለማከናወን የተቀመጡትን አቅጣጫዎችና የተጀመሩትን ስራዎች በመገምገም ይበልጥ መዳበር ያለባቸውን አቅጣጫዎች ያስቀመጠ ሲሆን የቀጣይ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ስራዎች እቅድና በጀቱን አፅድቋል፡፡

በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረትም የግንባሩ ስድስተኛ መደበኛ ጉባኤ እንደጠራ የወሰነ ሲሆን የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ሰይሟል፡፡

የስራ አስፀፈሚ ኮሚቴው ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ባለፉት ሶስት ወራት የነበሩትን የስራ አፈፃፀሞች በመገምገም በቀጣይ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ተግባራትን በሚመለከት ውሳኔ በማስተላለፍ እንደተጠናቀቀ ቃል አቀባዩ ገልጿል፡፡

# ፀረ-ድህነት ትግል ውስጥ የምሁራን ድርሻ ከፍተኛ መሆኑ ተገለፀ

ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማስፈን የወደቁ የህዝብ ልጆችን አደራ ለመወጣት በፀረ ድህነት ትግላችን ውስጥ የምሁራንና በየዘርፉ የሚገኙ ሙያተኞች ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ አቶ አዲሱ ለገሠ ገለፁ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የብአዴን ሊቀመንበር አቶ አዲሱ ለገሠ ይህንን የገለፁት በሸራተን አዲስ ታህሳስ 30 ቀን በተዘጋጀው 25ኛው የብአዴን የብር ኢዮቤልዩ ክብረ በዓል የእናመሰግናለን የእራት ግብዣ ላይ ነው።

በዚህ የምስጋና ዝግጅት ላይ አቶ አዲሱ ለገሠ ባደረጉት ንግግር የአማራ ሰማዕታት መታሰቢያ ሃውልት ከግንባታው እስከ ምረቃው በነበረው ሂደት የተሳተፉ ምሁራንም ሆኑ ሌሎች አካላት ያደረጉት ጥረት በፀረ ድህነት ትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

የአምባገነንነትና የአፈና ስርዓትን በመገ ርሰስ ሰላምና ዴሞክራሲን ያጎናፀፉን ሰማዕታት ደም በከንቱ እንዳልፈሰሰ የምናረጋግጠው የተያያዝነውን የፀረ ድህነት ትግል በልማት መስክ ዕድገትን በማስመዝገብ ስለሆነ የአገራችን ምሁራን በዚህ ረገድ ከፍተኛ ሃላፊነት አለባቸው ያሉት አቶ አዲሱ ምሁራኑ በቀጣይነት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ጥሪ አድርገዋል።

በዚሁ በእናመሰግናለን የእራት ግብዣ ላይ 25ኛው የብአዴን የብር ኢዮቤልዩ ክብረ በዓል በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር አስተዋፅኦ ላደረጉ እንዲሁም በሃውልቱ ግንባታ ውስጥ ለተሳተፉ ሰዓሊያን፣ አርክቴክቶች፣ መሃንዲሶች፣ የኮንስትራክሽን ድርጅቶችና የተለያዩ የግንባታ ባለሙያዎች ከአቶ ህላዌ ዮሴፍና ከአቶ አዲሱ እጅ የመታሰቢያ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

# ኢትዮጵያ በ5 ወራት ከ1 ቢሊዮን ብር በላይ የውጭ ሃብት አግኝታለች

ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ወራት ከተለያዩ የውጭ ሃገራት ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ብድርና እርዳታ ማግኘቷን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የህዝብ ግንኙነትና ጉባኤ አገልግሎት ሃላፊ አቶ ጌታቸው አድማሱ ሰሞኑን ለጋዜጣው ሪፖርተር እንደገለፁት ኢትዮጵያ ከነሃሴ 1997 ዓ.ም ጀምሮ ከተለያዩ የውጭ ሃገራት720 ነጥብ 42 ሚሊዮን ብር ዕርዳታና 565 ነጥብ 40 ሚሊዮን ብር ብድር አግኝታለች።

ከዚህም ሌላ ከቤልጂየም መንግስት 150 ነጥብ 82 ሚሊዮን ብር ዕዳ ሙሉ በሙሉ የተሰረዘላት መሆኑንም ሃላፊው አስረድተዋል።

የተገኘው የውጭ ሃብት ለምግብ ዋስትና፣ ለውሃ ሃብት ልማት፣ ለኤሌክትሪክ ሃይል፣ የምግብ እጥረት ላለባቸው እናቶችና ህፃናት መርጃ፣ ለሴፍትኔት ፕሮግራም የሚውል መሆኑን አቶ ጌታቸው ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የምታገኘው የውጭ ሃብት ፍሰት ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መምጣቱን የገለፁት አቶ ጌታቸው ይህም አገሪቱ ድህነትን በመቅረፍ የምዕተ አመቱን የልማት ግብ ለማሳካት የምታደርገው እንቅስቃሴና የምትከተለው የልማት አቅጣጫ በአለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው እንደሚያረጋግጥ ጠቁመዋል።

በ1997 ዓ.ም የበጀት አመት በአጠቃላይ 18 ነጥብ 13 ቢሊዮን ብር ብድርና ዕርዳታ ያገኘች ሲሆን 10 ነጥብ 13 ቢሊዮን ከመልቲ ላተራል ድርጅቶች፣ ቀሪው 8 ሚሊዮኑ ብር ከልማት ተባባሪ ለጋሽ መንግስታት መገኘቱን ሃላፊው አውስተዋል። በተጨማሪም በተጠቀሰው ጊዜ 14 ነጥብ 63 ቢሊዮን ብር ዕዳ የተሰረዘላት መሆኑንም ገልፀዋል።

የዕዳ ስረዛ ያደረጉ አገሮች ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ አሜሪካ፣ ጣሊያን፣ አውስትራሊያ፣ ፊንላንድ፣ ሩሲያ፣ ካናዳ፣ እንግሊዝና ስዊድን ሲሆኑ ከአለም አቀፍ ፋይናንስ ተቋማት ደግሞ አለም አቀፍ የልማት ማህበር፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ የአፍሪካ ልማት ፈንድ፣ የአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ፣ አለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ፣ ኖርዲክ ልማት ፈንድና አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት መሆናቸውን አቶ ጌታቸው አብራርተዋል።

በበጀት አመቱ ቀደም ሲል ከተፈረሙ ጥቅል የዕርዳታና ብድር ስምምነቶች ወደተግባር ለማሸጋገር የሚያስችሉ የ2 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ስምምነት ከዘጠኝ ለጋሽ መንግስታት ጋር መፈረሙን ሃላፊው ተናግረዋል።

በ1997 ዓ.ም በጀት አመት የተገኘው የውጭ ሃብት በአብዛኛው ለግብርናና ምግብ ዋስትና፣ አቅም ግንባታ፣ ለመንገድ፣ ለጤና፣ ለትምህርት፣ ለውሃ ሃብት ልማት፣ ለኢነርጂ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚውል መሆኑ ተገልጿል።

# አሁንም ህዝብና መንግስት እጅና ጓንት ናቸው

የሰሞኑ የአዲስ አበባ ከተማ ትኩሳት በአንዳንድ የከተማዋ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ግርግር ለመፍጠር የተካሄዱ ሙከራዎች ናቸው። እነዚህ ሙከራዎች ዋነኛ ኢላማቸው ያደረጉት የትምህርት ቤት ቁሳቁሶችን ነው። የመማሪያ ክፍሎች መስታወቶች፣ በአገር አቀፍ ደረጃ አንድና ወጥነት ያላቸው ትምህርቶችን በመስጠት ረገድ ምትክ የለሽነቱ የተነገረለት ትምህርት መስጫ ፕላዝማ ቴሌቪዥኖች ወዘተ ናቸው። በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ሌሎች ተማሪዎችን በአሳቻ ሁኔታ በድንጋይ መፈንከትም ተከስቷል።

እነዚህ በተለያዩ ቀናት በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተካሄዱ የሁከት ሙከራዎች የሚካሄዱት በትምህርት ቤቶች ውስጥ በአንዳንድ ተማሪዎች እንዲሁም ተማሪ ባልሆኑ ግን ደግሞ የትምህርት ቤቶችን ዩኒፎርም ለብሰው በገቡ ቅጥረኞች አማካይነት በመሆኑ ሙከራዎቹ ስፋትና ጥልቀት ያላቸው ሊሆኑ አልቻሉም። እንዲያም ሆኖ ግን በትምህርት ክፍለ ጊዜዎች አጠቃቀም ላይ እንዲሁም በትምህርት ቤት ንብረቶች ላይ ጉዳት ተከስቷል። እነዚህ ሙከራዎች ሙያውና ተሰጥኦው ሁከትና ግርግር መፍጠር ብቻ የሆነው የቅንጅት አክራሪ ሃይል መርሃ ግብር አካል ከመሆን የሚያልፉ አይደሉም። በዩኒቨርሲቲዎች (በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት)ና በጎዳና ላይ የተደረጉ ነውጦች በቢሊዮን የሚቆጠር ዋጋ ያለው የሃገርና የህዝብ ሃብት ወድሞ፣ የዜጎችን ህይወት ቀጥፎ፣ ለነውጠኞቹ አንዳችም ሳይጠቅም፣ እንዲያውም እንዲህ አይነት የለየለት ህገወጥነት በማያዳግም መልኩ እልባት ለመስጠት በቁጥጥር ስር ውለው በህግ እየተዳኙ ነው። በሰላም፣ በዴሞክራሲ፣ በልማትና በህገ መንግስቱ... ቀልድ እንደማይፈልጉ ኢህአዴግ ህዝብና መንግስት በቁርጠኝነት አረጋግጠዋል። ነውጠኞቹ ግን በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በኩል ያደረጉትን የመፍጨርጨር ኪሳራቸውን ለእህል ባልሰነፉ ለስራ ባልደረሱ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በኩል ለማካካስ ያደረጉት ሙከራም መክሸፍ።

የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የየትምህርት ቤቶቹ ሰፊ የተማሪ ሃይል የግርግር ተልዕኮ ከተቀበሉ ጥቂት ተማሪዎችና ቅጥረኞች ጎን ለመቆም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ነው። ከዚህም በላይ ሰፊው ሰላማዊ የተማሪ ሃይል አጥፊዎቹን አጋልጦ በመስጠትም የነውጥ ሙከራው ተባባሪ አለመሆኑን አረጋግጧል። በየትምህርት ቤቶቹ ተማሪዎች ወላጆች ሰሞኑን እየተካሄዱ ባሉ ውይይቶችም ምንም የማያውቁ ጨቅሎቻቸውን በፖለቲካ መሳሪያነት ለመጠቀም የሚደረገውን ሙከ ራም አጥብቀው የሚያወግዙ መሆናቸውን ነው ያረጋገጡት። በመንግስት ትምህርት ቤቶችን የሚገለገሉት በዋነኛነት የሰፊው የድሃው ህብረተሰብ ልጆች ናቸው። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚካሄዱ ጥቃቶች ተጎጂው ይሄው የህብረተሰብ ክፍል መሆኑን፣ እንዲህ አይነት የጥፋት ተግባራት በየትኛ ውም መስፈርት ውድመት እንጂ ለየትኛውም አይነት ጥያቄ መፍትሄ የማያመጡ መሆናቸው ላይ የተማሪ ወላጆች መክረዋል።

የአንድ ሰሞን የቅንጅት ለያዥ ለገናዥ የማስቸገር የሁከትና ነውጥ አካሄዱ አደብ እንዲይዝ በተደረገበት፣ ዴሞክራሲንና ህገ መንግስቱን እንጠረጠስ ካልሰደድን የወይ ፍንክች ቀረርቷቸው ፋይዳ ቢስ ሆኖ ከ109 የፓርላማ ተመራጮቻቸው 16ቱ በእስር፣ 17ቱ ደግሞ በይሉኝታ ወደ ፓርላማ ባይገቡም 76ቱ ፓርላማ በገቡበት ሁኔታ የሰሞኑ የቅንጅት በጨቅላ ተማሪዎች ክንድ የዘንዶ ጉድጓድን የመለካት ሙከራ ይህ ሃይል ከፖለቲካዊ ኪሳራው ትርፍ የመፈለግ እብደቱን የሚያመላክት ብቻ ግን አይደለም። ሰፊው ህዝብ፣ መንግስትና መሪ ፓርቲው ኢህአዴግ በትምህርት ዙሪያ ከሚያደርጉት ልማት ፊፅሞ በተቃረነ ማጥ ውስጥ የተዘፈቀ መሆኑን የሚያሳይም ነው።

ኢህአዴግ ፈጣን የትምህርትና ስልጠና ዕድገትን አልሞ ህዝቡን በሰፊው በሚያሳትፍ የሰው ሃይል ልማት ላይ የሰጠው ትኩረት ጥያቄ ውስጥ የሚገባም አይደለም። አገር አቀፉን የትምህርት ተቋማት ግንባታ ዕድገት

እንኳን ትተን የመዲናችንን የመንግስት ትምህርት ግንባታ ዕድገት ካለፈው አመት ትምህርት ቤቶች ተገንብተዋል፡፡ በነባር ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በተካሄዱ የማስፋፋት ስራዎች 2ሺህ 525 የመማሪያ ክፍሎች ያሏቸው 101 ህንፃዎች ተገንብተው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ኢህአዴግና የአዲስ አበባ አስተዳደር የፈረቃ ትምህርትን ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት ደፋ ቀና በሚሉበት ወቅት የተማሪ የክፍል ጥመርታን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከ70-80 የነበረውን ወደ 56 ዝቅ እንዲል ሲያደርጉ በተመሳሳይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪ የክፍል ጥመርታን ወደ 67 እንዲወርድ አድርገዋል፡፡ የቅንጅት ነውጠኛ ሃይል ይህን የልማት፣ ዜጋን የመቅረፅ ጥረትን በኃዳና ነውጥና በትምህርት ቤቶች ውስጥ ሁከት ለማውደም ነው የሞከረው፤ ሙከራው በራሱ ትልቅ ኪሳራና ውድመት ያስከተለም ነው፡፡

የአዲስ አበባ አስተዳደር በሰሞኑ በተማሪዎች አማካይነት በትምህርት ቤቶች ንብረት ላይ የደረሰውን ውድመት ተከትሎ በራሱ ለመጠገን አቅሙም ጊዜውም ሆነ ፍላጎቱ የሌለው መሆኑን በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ይህ አቋም በመሰረቱ ማን ያፈረሰውን ማን ይገነባል ከሚል ተራ አስተሳሰብ የተነሳ አለመሆኑም መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ወላጆች በየትምህርት ቤቶች ውስጥ ባካሄዱት ውይይት የአዲስ አበባ አስተዳደር ቀጣይ ጥረትን በውል አጢነው የወደሙትን ለመተካት፣ የጎበጡትን ለማቃናት የተስማሙበት ሁኔታ ተጠቃሽ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቀጣይ ጥረት በሁከት የተሰባበሩ የትምህርት ቤት ንብረቶችን ከመጠገን የላቀ የቤት ስራ ያለው መሆኑ ይህን ድርሻ ለወላጆች ለመተው መገደዱም እውነትነት አለው፡፡ በወርሃ ጥር የአዲስ አበባ አስተዳደር አስቀድሞ ባስቀመጠው ዕቅድ መሰረት የፈረቃ ትምህርትን ሙሉ በሙሉ የሚያስቀርበትን የተማሪ ክፍል ጥመርታን ደረጃውን የጠበቀ የማድረግ ዕቅዱን የሚያገባድድበት ተጨማሪ አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን የመገንባት በነባሮቹ ውስጥም የማስፋፋት ስራውን እንደሚቀጥል አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት አምስት ሺህ ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎችን ያስገነባል፣ የዚህ ወጪ ደግሞ 100 ሚሊዮን ብር ከመንግስት፣ 33 ሚሊዮን ብር ደግሞ ከህዝብ ተገኝቷል፡፡

ይህን የሰሞኑን የትምህርት ቤቶች ግርግር ወላጆች ተማሪዎች እንዲሁም የተለያዩ የሰላምና ልማት ማህበራት አውግዘውታል፡፡ ከዚህ ባሻገርም በትምህርት ቤቶች ውስጥ የውይይት መድረክ ከፍተው የትምህርት ቤት ማህበረሰብን የማወያየት ዕቅድ ያላቸው ማህበራት መኖራቸውም ተስተውለዋል፡፡ ይህ አንድ አዎንታዊ እርምጃ ነው፡፡ በቀጣይነት የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቤቶች የወላጅ መምህር ህብረት በየትምህርት ቤቱ ህብረተሰቡን ያሳተፈ ጠንካራ ተግባራት ማከናወን የሚገባቸው ናቸው፡፡ የቅንጅት ነውጠኛ ሃይል የሃገር የህዝብ እንዲሁም ተተኪውን ትውልድ በመቅረፅ ረገድ የለየለት አሉታዊ ሚና የሚጫወት መሆኑን በማያጠራጥር ሁኔታ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ ህዝብና መንግስት እንዲሁም መሪው ፓርቲ ኢህአዴግ በተለያዩ የህግ አግባቦች ይህን መሰል የሁከት የውድመት ድርጊትን ከመከላከል እንዲሁም ምንጩን ከማድረቅ አንፃር ዛሬም እንደትናንቱ እጅና ጓንት ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል፡፡

በሰሞኑ የትምህርት ቤቶች ውስጥ ግርግር ቀጥታ ተሳታፊ የነበሩ ዩኒፎርም ለብሰት ገብተው ሲያውኩ የነበሩ 22 ቅጥረኞችን ከአሰማሪዎቻቸው ጋር ህዝብና መንግስት ተባብረው በቁጥጥር ስር ማዋላቸውም መልካም ጅምር ነው፡፡

## ርዕሰ አንቀፅ

# ጠንካራ ውስጣዊ ልማት ለአበረታች የውጭ ድጋፍ

በኢህአዴግ መሪነት የተጀመረው የልማትና የዴሞክራሲ ተግባር በሃገር አቀፍ ደረጃ የተሻለ ለውጥን በአለም አቀፉ ህብረተሰብ ዘንድም አድናቆት እየተቸረው ይገኛል:: ለዚህም አለም አቀፍ ተቋሞችና ድርጅቶች ከሚሰጡት ተስፋ ሰጭ አስተያየት በተጨማሪ የተለያዩ የማበረታቻ እርምጃዎችን እየወሰዱ ይገኛሉ::

ባያዝነው የ1998 ዓ.ም የበጀት አመት ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ ሃገራችን የተለያዩ ዕርዳታዎችን ያገኘች ሲሆን የዕዳ ስረዛም እንደተደረገላት መረጃዎች ያመለክታሉ:: ባለፉት ስድስት ወራት 150 ነጥብ 82 ሚሊዮን ብር ዕዳ የተሰረዘላት ሲሆን 720 ነጥብ 42 ሚሊዮን ብር ዕርዳታ አግኝታለች:: 565 ነጥብ 40 ሚሊዮን ብር ብድርም ተሰጥቷታል:: በቅርቡ ይፋ የሆነው መረጃ ደግሞ እንደሚያመለክተው አለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም አይ.ኤም.ኤፍ 161 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የኢትዮጵያን ዕዳ ሰርዟል:: ይህ በእ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 2005 በፊት ያለውን እንደሚመለከትም ይፋ ሆኗል::

የሁሉም የዕርዳታና የብድር ስምምነቶች እንዲሁም የዕዳ ስረዛዎች ምክንያት በጥቅሉ ኢትዮጵያ በተጨባጭ በድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ላይ እያሳየችው ካለው ለውጥ ጋር የተያያዘ ነው:: ግብርና መር የኢንዱስትሪ ፖሊሲውን ተግባራዊ በማድረግ በኩል ወደውጭ የሚላኩ ዕቃዎች በከፍተኛ ሁኔታ መጨመራቸውም ለማበረታቻው ምክንያት ሆኗል:: አሁን ካለው የማክሮ ኢኮኖሚ ሂደት ጋር የተጣጣመ ፖሊሲ በመቅረፅና የኢኮኖሚ መረጋጋት እንዲኖር በማድረግ፣ የገንዘብ አጠቃቀም አመራርን በማጎልበትና የውስጥ ቁጥጥርና ኦዲት አካሄድን ማጠናከሯ የሃገር ውስጥ ኢኮኖሚ ሁኔታው እየተሻሻለ፣ ያረጋገጠው ውጤት እየጨመረና እየጎለበተ በመሄዱ ያለፉት አመታት መረጃዎች በቂ ምስክሮች ናቸው:: በተለይም አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም እየወሰደው ላለው የማበረታቻ እርምጃ ተጠቃሽ ነው::

ይህንን የልማት ሂደትን ማረጋገጥ የተቻለው ፊት ለፊት የተጋረጠውን ችግር በመጋፈጥና በመፍታት ነው:: በተለይም የልማት፣ የሰላምና የመልካም አስተዳደር ሁኔታን ምቹና የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችለውን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ስርአት ለመቀልበስ የሚጥሩትን ሃይሎች በተግባር በመመከት ነው:: በአለም አቀፍ ደረጃ ምስክርነት የተሰጠውን ዕድገት እያጨለሙና እያዛቡ፣ የሃገር ውስጥ የልማት አቅምንና ዕድገትን ለማደፍረስ ብቻ ሳይሆን የውጭ እርዳታና ብድርን ለመግታት የሚሯሯጡ የአንዳንድ ሃይሎችን ድርጊት በዘላቂነት መግታት የተጀመረውን ተስፋ ሰጪ ዕድገት ለማገዝለቅ የሚረዳ ነው::

በመሆኑም ልማታችን በህዝቡ ሰፊ ተሳትፎ እየጎለበተ እንዲቀጥል፣ ከዚህ ጋር የተያያዘውና በውስጥ ጥንካሬያችን ላይ የተመሰረተው የውጭ ድጋፍና ዕርዳታ እንዲጠናከር፣ ሰላምና ዴሞክራሲያችንን መጠበቅ ይገባል:: ድህነትን ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረትና የሚወጣው ዕቅድ ተግባራዊ እንዲሆን በየግል መንሳሳት ብቻ ሳይሆን በጋራ ማበርም ያስፈልጋል:: ይህንን የጋራ የልማት ሃይል ለመበተን የሚጥሩትን ሃይሎች በማስታገስ መቀጠል የማይታለፍ ተግባር ነው:::

## ትኩረት

# የውጭ ድጋፍ ለሃገር ውስጥ ልማት

ሃገራችን የምታካሂደውን ግብርናን ማዕከል ያደረገውን ልማት ለማፋጠን በተጨባጭ ያለውን የህዝብ ጉልበት፣ ውሃና መሬት አስተባብሮ ለዕድገት መብቃት እንደሚቻል ባለፉት ጥቂት አመታት ብቻ በተደረገው እንቅስቃሴ ውጤታማነቱን ማየት ተችሏል:: ይህንን የተጀመረውን ውጤታማ የልማት ጉዞ ለማዝለቅ አሁንም የሃገር ውስጥ ሃብት ላይ መመስረት ወሳኝ መሆኑ ግልፅ ነው::

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከውጭ የሚገኝን ሃብት ማሰባሰብና በአግባቡ መጠቀም እንደኛ ካለ ድሃ አገር የሚጠበቅ የማይታለፍ ተግባር ነው:: በዚሁ መሰረት ባሳለፍነው 1997 ዓ.ም የውጭ ሃብትን ለማሰባሰብ በተደረገው እንቅስቃሴ የቆዩ ዕዳዎችን በማሰረዝና ብድር በማግኘት የተሻለ ርቀት መሄድ እንደተቻለ ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያሳያል::

ከለጋሽ መንግስታት ጋር የሚደረጉት የኢኮኖሚ ልማት ትብብር ስምምነቶች አካሄድን ስንመለከት በቅድሚያ ከሶስት እስከ አምስት አመት የሚደርስ አጠቃላይ የትብብር ማዕቀፍ ይፈረማል:: በመቀጠልም ይህንኑ መነሻ በማድረግ በየአመቱ ወደ ተግባር ለማሸጋገር የሚያስችል ስምምነት ይደረጋል::

ይህንን አጠቃላይ አካሄድ መነሻ በማድረግ ኢትዮጵያ ባለፈው አመት 16 ነጥብ 63 ቢሊዮን ብር (1 ነጥብ 67 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር) ዕዳ ተሰርዞላታል:: ከዚህ በተጨማሪም ከአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት በተጠቀሰው ጊዜ 729 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር (84 ነጥብ 03 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) የዕዳ ቅነሳ ተደርጎላታል:: በ1998 ዓ.ም የበጀት አመትም ባለፉት ስድስት ወራት 150 ነጥብ 82 ሚሊዮን ዕዳ ተሰርዞላታል:: በተጨማሪም ሃገራችን በአመቱ ካገኘችው የውጭ ሃብት ውስጥ 9 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር (10 ነጥብ 06 ቢሊዮን ዶላር) እርዳታ፣ ቀሪው 8 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር (1 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር) ብድር እንደሆነ መረጃዎቹ ያመለክታሉ:: በአንፃሩ ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ 720 ነጥብ 42 ሚሊዮን ብር ዕርዳታ ያገኘች ሲሆን 565 ነጥብ 40 ሚሊዮን ብር ብድር አግኝታለች::

በአጠቃላይ በ1997 ዓ.ም በጀት አመት የተገኘው የውጭ ሃብት ከ1996 በጀት አመት ጋር ሲነፃፀር ከእጥፍ በላይ እንደጨመረ መረጃዎች ያስረዳሉ:: ይህ እያደገ በመሄድ ላይ ያለውን የውጭ ሃብት ግኝትና የዕዳ ስረዛውን መነሻ ምክንያትና ውጤቱን ማየት እየተከተልነው ያለውን የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታን ተስፋ ሰጪነት ለማየት የበለጠ ይረዳልና ወደዚያው እናምራ::

ኢትዮጵያ በከፍተኛ ድህነት ውስጥ ከሚገኙት ሃገሮች ውስጥ አንዷ ናት:: የምግብ ዋስትና ባለመረጋገጡ ምክንያት በከፍተኛ የምግብ እጥረት የሚንገላቱ አካባቢዎች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም:: የስራ አጥነት ደረጃውም ከፍተኛ ነው:: ሌሎች የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው:: በተለይም ደግሞ ባለፉት ስርአቶች በነበረው የጦርነት ፖሊሲ ምክንያት ረዘም ላለ ጊዜ ይህ ነው የሚባል የለውጥ ጭላንጭል ያልታየባት፣ ዕድገት የረሳት ሆና ቆይታለች - ኢትዮጵያ::

አምባገነኑና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ የሆነው የደርግ መንግስት ከተደመሰሰ በኋላ ለዕድገት መሰረት የሆነው የዴሞክራሲና የሰላም ብርሃን መብራት ችሏል:: መስራት የሚችሉ እጆች መንቀሳቀስ፣ የተዘጉ አንደበቶች ሃሳብ ማመንጨት፣ የጀመሩትም ይህንኑ ለውጥ ተከትለው ነው::

በተለይም ህገ መንግስት ፀድቆ ህዝቦች በማንነታቸው ኮርተው ራሳቸውን በራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት ስርአትመመስረቱ እውን ሲሆን፣ እውነትም ኢትዮጵያ የሁሉም መሰባሰቢያ ጎጆ መሆኗን ብሔሮችና

ብሄረሰቦች አረጋግጠዋል። የእኩልነታቸውና የአንድነታቸው ምሰሶ የሆነውን ህገ መንግስትን መሰረት በማድረግም ለመስ ራትና ለውጥ ለማምጣት ዝግጁነታቸውን ለማሳየት ጊዜ አልወሰደባቸውም።

ይህንን የተቀየረ ሁኔታ በመጠቀም ህዝቡን አደራጅቶ የተሻለ የስራ ባህልን መገንባት እንደሚቻል ያረጋገጠው ኢህአዴግ የሃገሪቱን ሁኔታ ያገናዘቡ እቅዶችን እያወጣ በመንቀሳቀስ በየጊዜው ብቅ ብቅ ያሉ እና ለምሳሌነት የሚጠቀሱ ተጨባጭ እና ፈጣን ዕድገትን ያመላከቱ ለውጦችን ማረጋገጥ ችሏል። ቀስ በቀስም የተጠናከሩ ስትራቴጂና ፖሊሲዎችን ያወጣ ሲሆን በተለይም ገጠሩን ማዕከል ያደረገ ግብርና መር የልማት ስትራቴጂን በማውጣት የተደራጀ፣ ሰፊ፣ ቀጣይነት ያለው አስተማማኝ ልማትን ለማረጋገጥ መሬት የያዘ ስራ መስራት ተጀምሯል።

ገጠርን ማዕከል ያደረገው የልማት ስትራቴጂ ከሁሉም በላይ የሃገራችንን ሁኔታ በማገናዘብ አርሶ አደሩ ያለውን ጉልበት፣ መሬትና ውሃን በአግባቡ በመጠቀም ላይ የተመሰረተ መሆኑ ትልቁና ዋናው ጉዳይ ነው። ይህ አብዛኛውን አርሶ አደር በማቀፍ፣ በአብዛኛው አካባቢ ላይ ለውጥን ማረጋገጥ የሚችል መሆኑ ዕድገቱን ፈጣን ብቻ ሳይሆን አስተማማኝ ያደርገዋል። በመሆኑም በኢህአዴግ መሪነት ሃገራችን እየተከተለችው ያለችው የገጠር ልማት ስትራቴጂ ፈጣን ልማትን ለማረጋገጥ ያለመ፣ አርሶ አደሩን በስፋት ያሳተፈና አብዛኛውን የገጠር አካባቢ በመለወጥ የምርት እድገትን ማረጋገጥ የሚያስችል ሆኖ እየቀጠለ ይገኛል።

ይህ የልማት ለውጥ የተመሰረተበት መልካም አስተዳደርም በየደረጃው ተያይዞ እየተከናወነ ያለ ስራ ነው። የሚረጋገጠውን ልማትና ውጤት በሃላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ ማየት፣ ያለውን ውስን ሃብት በቁጠባና በአግባቡ መጠቀም፣ ፈጣን አገልግሎትን መስጠት፣ ሁሉንም የልማት ስራዎች በየደረጃው ባለ የህዝብ ተሳትፎ ማጠናከር የመሳሰሉት ጉዳዮች ከልማቱ ጋር የተገናዘቡና አብረው ዕድገትን እያፋጠኑ የሄዱ ግብአቶች ናቸው።

በተያያዘ ሁኔታ እነዚህን ከላይ የተገለጹትን ተግባራት ለማጣመር የሚያስችለው የአቅም ግንባታ ተግባር የህዝቡንም ሆነ በአጠቃላይ የህብረተሰቡን አስተሳሰብ በዕድገትና በለውጥ ላይ መመስረት እንዲችል በማድረግ ተጠናክሮ እየቀጠለ ይገኛል። የአሰራርና የአደረጃጀት ጉዳይም ትኩረት ተሰጥቶታል።

ወደተነሳንበት ነጥብ ስንመለስ እነዚህ በሃገር ውስጥ አቅም ላይ ተጀምረው እየተገነቡ እና ወደፊት እያመሩ ያሉት ተግባ ራት ለሃገራችን ለውጥና ለዕድገቱ አስተማ ማኝነት ወሳኝ ናቸው። እነዚህ ተግባራት ናቸው ለፈጣን ዕድገት መሰረትና ለበለጠ ለውጥ መነሻዎች ሆነው እያገለገሉ ያሉት።

የሃገራችን የልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ አካሄድን ለማጠናከር የሚከናወነው የውጭ ግንኙነት ስራ ከሚታየው የልማት ለውጥ ጋር ተዳምሮ የእርዳታና የብድር ድጋፍ እንድናገኝና የዕዳ ስረዛ እንዲደረግ መሰረት ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ። ለምሳሌ በ1997 በጀት አመት ከተገኘው የውጭ ሃብት በአብዛኛው ለግብርናና ምግብ ዋስትና፣ አቅም ግንባታ፣ ለመንገድ፣ ለጤና፣ ለትምህርት፣ ለውሃ ሃብት ልማትና ለኢነርጂ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ ነው እየዋለ ያለው። ከአመት አመት በእጥፍ እያደገ ያለው የውጭ ሃብት ድህነትን በመቅረፍ የምዕተ አመቱን የልማት ግብ ለማሳካት ለሚደረገው እንቅስቃሴ መዋሉ የተያዘው የልማት አቅጣጫ በአለም አቀፍ ህብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት እያረጋገጠ መሄዱን ያረጋግጣል።

የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የዕድገት አካሄድ ባይኖረንና ፖሊሲና ስትራቴጂው ወደውጤት የሚመሩ ባይሆኑ ኖሮ የሃገራችን ልማት፣ የውጭ ሃብትም ውጤታማ ባልሆነ ነበር። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሩቅ ሳንሄድ ያለፈውን ስርአት በማየት ማረጋገጥ ይቻላል።

ደርግ የሃገራችንን አብዛኛውን ህዝብ የያዘ፣ አቅምን ያገናዘበ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ያልገነባ ፀረ ህዝብ መንግስት በመሆኑ የጦርነት እንጂ የልማት መሪ መሆን አልቻለም። ስለዚህ አብዛኛውን ህዝብ ለልማት ማሰለፍ ሳይሆን በግዴታ ለጦርነት ለማሰለፍ ባዝኗል፤ ይህንን ተግባሩን ለማሳካት ያግበሰብስ የነበረውን

ዕርዳታ ደግሞ ለጦርነት ግብአት በመግዛት ላይ አውሎታል። ስለዚህ የሃገር ውስጥ የዕድገት አቅጣጫ ሲዛባ የውጭ እርዳታም አወጣጡም ይሁን ውጤቱ መዛባቱ የግድ ሆኗል።

በአንፃሩ የኢህአዴግ መንግስት ከሃገራችንና ከህዝቡ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ፖሊሲና ስትራቴጂ በማውጣት ህዝቡን በዙሪያው ማሰባሰብ ችሏል፣ ከልማቱ ተጠቃሚ ስለሆነ በየወቅቱ ተነሳሽነቱ እየጨመረ ህይወቱን እያሻሻለ፣ የአካባቢውን ብሎም የሃገሪቱን ልማት እያፋጠነ ይገኛል። ይህ በውስጥ የሚከናወነውን ተግባር ለመደገፍ የሚካሄደው እርዳታ ሲጨመርበት ደግሞ ፍጥነቱ ይጨምራል።

በአጠቃላይ በ1997 በጀት አመት ሃገራችን ያገኘችው የውጭ ሃብት መነሻ በሃገር ውስጥ የሰራነው ስራ ነው። አሁንም ዕድገቱን ለማዝለቅ ከሃገር ውጭ ሃብት ማሰባሰብ የማይታለፍ ተግባር ቢሆንም የሃገር ውስጥ ስራው ወሳኝና መሰረታዊ ነው።

እናም የውጭ ግንኙነት ስራችን በሃገራችን የዴሞክራሲ፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ግንባታ ስራ ላይ እንደተመሰረተው ሁሉ ስራውን ለማጠናከርና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚሰራው ስራም ከሃገር ውስጡ ጋር ተያይዞ መቀጠል ይኖርበታል። የሃገራችን የወደፊት ብሩህ ገፅታን የሃገር ውስጥ ተግባርን ሊደግፍ በሚችል የውጭ ስራ መታገዙ መበረታታት ይኖርበታል።

## እኛና እነሱ

# እያንዳንዷ ቀን ለሰላምና ለልማት

የነጠረ አላማና ግብን ይዞ የተሰለፈው ኢህአዴግ ህዝቡን በማስተባበር በ1980ዎቹ ባደረጋቸው መጠነ ሰፊ ጥቃቶች የደርግን መንግስት ለማንኮታኮት ችሏል።

በዚህ ወቅት ኢህአዴግን ያስጨነቀው ጉዳይ ቢኖር የደርግ መውደቅ ሳይሆን ደርግ ከተገረሰሰ በኋላ የሚኖረው የሀገሪቷ መፃኢ እድል ነበር።

ምክንያቱም አንዱ በወቅቱ ከ17 በላይ የታጠቁ የብሔረሰብ ነፃ አውጪ ድርጅቶች በአፈና ተይዘው ስለቆዩ የደርግን የመደምሰስ አጋጣሚ በመጠቀም የመበታተን አደጋ እንዳይ ደርስ ከፍተኛ ስጋት መፍጠሩ በተንታኞችም ጭምር ይገለፅ የነበረበት ወቅት በመሆኑ ነው።

ሆኖም ኢህአዴግ በወቅቱ የወራት እድሜ የነበረውን የደርግ መንግስት ለመደምሰስ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ በትጥቅ ትግል ውስጥ የተሰማሩትን ሃይሎች በማሰባሰብ በቀጣይ የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ላይ ግልጽነት ለመያዝ የሚያስችል ስትራቴጂ ተከትሏል።

በሂደትም በሀገር ውስጥና በውጪ አገራት ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ ከነበሩ የፖለቲካ ሃይሎች ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል ስምምነት መፈረሙ ይታወሳል።

ከዚህ የጋራ ስምምነት በኋላም በአጭር ጊዜ ውስጥ የደርግን ግብአተ መሬት በማጠናቀቅ ሁሉንም የሀገሪቷን ህዝቦች የሚወክሉ ተሳታፊዎች በተገኙበት የሽግግር ወቅት ቻርተርን በማጽደቅ ፍትሐዊ የውክልና ስርአት እውን እንዲሆን ኢህአዴግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።

ኢህአዴግ ደርግን ለመደምሰስ ለከፈለው መስዋዕትነት የተለየ ወሮታን ሳይጠይቅና ለስልጣን ሳይሰስት በሽግግር ወቅት በነበሩት የሃላፊነት ቦታዎች ሳይቀር ፍትሐዊ የስልጣን ክፍፍል ማድረጉ ከማንኛውም ዜጋ የሚሰወር ጉዳይ አልነበረም።

ከዚህ በኋላም ህዝባዊ መንግስት እንዲቋቋም ገና ከመነሻው የታገለለትን ጽኑ አቋም እውን ለማድረግ የሚያስችሉ ምርጫዎች እንዲካሄዱ በማድረግ በህዝብ ይሁንታ ብቻ ስልጣን የሚያዝበት አስተሳሰብ በሀገሪቷ ገቢራዊ እንዲሆን አድርጓል።

ሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች የሀገሪቷን ህግና ስርአት አክብረው በሰላማዊ መንገድ ያለምንም ገደብ የፖለቲካ አቋማቸውን እንዲያንፀባርቁ በማድረግ ህዝቡ የተለያየ አማራጮችን አግኝቶ ይበጀኛል የሚለውን የፖለቲካ ሃይል ወደ ስልጣን የሚያመጣበት ስርአት ተዘርግቷል።

ለብሔራዊ ማንነታቸውና ለመብታቸው በተለያዩ መልኩ ሲታገሉ የቆዩት ብሔረሰቦች ዛሬ ሁለንተናዊ ጥያቄዎቻቸው ምላሽ በማግኘቱ አንድ የጋራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። ዛሬ በፍላጎታቸው የመሰረቱትን አንድነት በማጠና ከር ዋነኛ ጠላታቸው የሆነውን ድህነትን ለመቅ ረፍ የየበኩላቸውን ርብርብ እያደረጉም ነው።

የሀገሪቷ ተጨባጭ ሁኔታ ይህን ሲመስል በአንፃሩ የተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎች በዚሁ እውነታ ላይ ያላቸው አቋምና በሀገሪቷ መፃኢ እድል ላይ ሊጫወቱ የሚፈልጉት አሉታዊ ተግባር ምን እንደሆነ እንመልከት።

ለረዥም አመታት የትጥቅ ትግል የጀመረ ቢሆንም በያዘው አላማ የሚፈለገውን የህዝብ ድጋፍ ሊያገኝ ያልቻለው ኦነግ በሰላማዊ መንገድ አላማውን እንዲያራምድ በሽግግር ወቅት የተመቻቸለትን እድል ረግጦ በመውጣት ወደ ተራ አሸባሪነት ተግባር መሸጋገሩ አይዘነጋም።

በ1994 ዓ.ም በመላው ኦሮሚያ ክልል ጦርነት በማወጅ ከሽግግር መንግስቱ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ የሚፈለገውን ድጋፍ በማጣቱ የሰውን ህይወት በማጥፋት፣ የህዝብንና የመንግስትን ንብረት ከማውደሙም ባሻገር የኢትዮጵያም ሆነ የኦሮሞ ህዝቦች ታሪ ካዊ ጠላት የሆነው የሻዕቢያ መንግስት ተልዕኮ አስፈፃሚ በመሆን በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

ባለፉት 14 አመታት ውስጥ በአዳማ፣ በሻሸመኔ፣ በአዲስ አበባ የህዝብ መገልገያ በሆኑ የተለያዩ ሆቴሎች ላይ ፈንጂ በመቅበር 34 ሰዎችን በማቁሰል ንብረት አውድሟል።

በሀረርና በአርሲ ህዝቡን እርስ በርሱ በማጋጨት ለ32 ሰዎች ህይወት መጥፋት ለ138 ሰዎች መቁሰል እና በብዙ ሚሊዮን ብር ለሚገመት ንብረት ውድመት ምክንያት ሆኗል።

በጨለንቆ፣ በሐረርጌ እስከነፍ ሳቸው ሰዎችን በመቅበር ዘግናኝ የጭካኔ ተግባራትን ከመፈፀሙም በላይ በበደኖም የበርካታ ዜጎች ህይወት በአሳዛኝ ሁኔታ እንዲያልፍ ማድረጉ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

በአሁኑ ወቅትም በተለያዩ በኦሮሚያ ከተሞች አካባቢ ጨቅላ ህፃናትን በተለያዩ መንገዶች ለአፍራሽ ተልዕኮው ማሳኪያነት እየተጠቀመባቸው ይገኛል። የሀገሪቷ ታሪካዊ ጠላት ከሆነው የኤርትራ መንግስት በሚደረግለት የገንዘብ ድጋፍ በመታገዝ እታገልለታለሁ የሚለውን የኦሮሞ ህዝብ ልጆች ህይወት በመቅጠፍና የአገልግሎት ተቋሞቻቸውን በማውደም ላይ ይገኛል።

ኦነግ በቀቢፀ ተስፋነት የጀመረው የሽብር እና ከውጪ ጠላት ጋር በማበር የሚፈጽመው ተግባር ይበልጥ ከህዝቡ ሊያቆራርጠው ካልሆነ በስተቀር የሚያስገኝለት እንዳችም ፋይዳ እንደሌለው ህሊና ያለው ዜጋ ሁሉ የሚገነዘበው ጉዳይ ነው።

ሆኖም በተለያዩ የውጪ አገራት የሚንደላቀቁና ወላፈኑ የማይነካቸው የኦነግ መሪዎች ድርጅቱ በህይወት ከሌለ የራሳቸው ህልውና ጥያቄ ውስጥ ስለሚገባና የኢትዮጵያን እድገትና ተስፋ ከማይሹ ወገኖች የሚያገኙት ፍርፋሪ እንዳይቀርባቸው የጥፋት ሃይሎች መሳሪያና ጉዳይ አስፈፃሚ በመሆን እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ።

በነገራችን ላይ የኦሮሞ ህዝብ ራሱን በራሱ ማስተዳደር አለበት፤ ከኢትዮጵያ ጋር አብሮ መኖር የለበትም መገንጠል አለበት፤ የሚል የከረረ አቋም እንዳለው የሚገልፀው ኦነግ የኦሮሞ ህዝብ ያገኛቸውን መብቶችና ጥቅሞችን ለመንጠቅ በይፋ የሚንቀሳቀሱ የቅንጅት አመራሮችን በምርጫ ወቅት መደገፉ ማንነቱን ይበልጥ አጋልጦታል።

በመሆኑም የኦነግ አመራሮች ኑሮአቸውን ለመግፋትና ከጠላቶቻችን የሚያገኙት ፍርፋሪ እንዳይቀርባቸው በሀገር ውስጥ ህዝቡ እርስ በርሱ መታመስ አለበት፤ ሰላምና ዴሞክራሲ እንደሌለ በውጪ አገራት መገለጽ አለበት በሚለው አስተሳሰብ እየገፉበት ይገኛሉ።

እጅግ በጣም የሚገርመው ጉዳይ ደግሞ በውጪም ሆነ በሀገር ውስጥ ለኢትዮጵያ «አንድነት» ይፈሳል ደማችን እያሉ የሚፎክሩ ተቃዋሚ ሃይሎች አንድም ጊዜ ይህንን የኦነግን ጨለምተኛ አስተሳሰብና ተግባር ሊኮንኑ አለመቻላቸው ነው።

እነዚህ ሃይሎች በህዝብ መገልገያ ተቋማት ላይ ውድመት ሲደርስ፣ የሰው ህይወት ሲጠፋ፣ ሰላም ሲደፈርስ ኢህአዴግ የተጎዳ እየመሰላቸው በዜጎች ቁስል ላይ እንጨት ከመስደድ ሊታቀቡም አልቻሉም። በመሆኑም ወይ ለይቶላቸው የኦነግ ድርጊትም ፍትሐዊና ህጋዊ በመሆኑ የትግል አንድነታችንን እናጠናክራለን ብለው በይፋ ለመግለጽ አልደፈሩም። አለያም ደግሞ በያዙት የሃይል አንድነት ላይ የፀና አቋም ካላቸውም

በይፋ ይህ ተግባር የኢትዮጵያን አንድነት የሚያፈርስ ነው ብለው በአደባባይ ከመግለጽ የተቆጠቡበት የፖለቲካ ቁማር ከሁሉም ዜጋ የሚሰወር አይደለም።

በአሁኑ ጊዜ ፓርላማ የገቡ ተቃዋሚ ሃይሎችም ቢሆኑ የኦነግን የሀገር ከሃዲነት ድርጊት ከማውገዝ ይልቅ መንግስትንና ኢህአዴግን ለመኮነን የሚጣደፉበትን ሁኔታ እያየን ነው። ሲጠቃለል በአገራችን ውስጥ ያለው የሃይል አሰላለፍና ህዝባዊ ወገናዊነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ፈጦ ወደመጣበት ደረጃ ደርሰናል። ከፊታችን የተደቀኑት ሁለት አማራጮች ብቻ መሆናቸው ገሃድ ሆኗል።

የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ መንገድ፣ በሌላ በኩል ለጭፍን ስልጣን ፍላጎት አገርንና ህዝብን የሚጎዳ ጥፋት መንገድ ናቸው። ምርጫው የእያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ህዝብ ነው። መቼም ቢሆን ለአገርና ለወገን የሚቆረቆር ዜጋ የጥፋትን መንገድ ሊመርጥ አይችልምና እያንዳንዱ ህሊናውን ይፈትሽ ዘንድ ጊዜው አሁን ነው።

ከጥፋት ሃይሎች ጋር በመሰለፍ አገርንና ወገንን በመበደል ታሪክ ይቅር የማይለውን ጥፋት ከመስራት ታቅቦ ለሀገርና ለወገን ጠቃሚ ስራ በመስራት ታሪክ ሰርቶ ማለፍ ይገባል። ከዚህ በመለስ ሽብርን እየዘሩ ህዝቡ ተረጋግቶ በመልካም አስተዳደር ስርአት ግንባታና ድህነትን በመቅረፍ የሚፈልግበትን ርብርብ እንዳያደርግ ሰላም የሚነሱ ሃይሎች ከአሁን በኋላ እድል ሊሰጣቸው አይገባቸውም።

ራሳቸው ወላፈኑ በማይደርስበት ቦታ ተቀምጠው የጥፋት ሃይሎችን እያሰማሩ ሰላምና መረጋጋትን ለማሳጣት የሚንቀሳቀሱ ሃይሎችን በተመለከተ ህዝብ፣ መንግስት እና ኢህአዴግ ተቀናጅተው ሊያስታግሷቸው ይገባል እንላለን።

እያንዳንዷ የሰላም ቀን ከድህነት ለመውጣት የምናደርገውን ፍጥነት ስትጨምር እያንዳንዷ የሁከትና የብጥብጥ ሰአት ድህነትንና ኋላቀርነትን ታራዝምብናለችና።